| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ድርሰት ። |
| ርእስ ፤ | "ጦማረ ፡ ክዋኔ ፥ 3 ኛ ፦ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ እንመሥርት !" |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 2017 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፡ ቍ.2017-003 |
| ማስታወሻ ፤ | "ክዋኔ" ፡ ዐምድ ። |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ክዋኔ

CONSTITUTION | دستور

*[በዚህ ፡ ዐምድ ፥ ስለ ፡ ክዋኔ ፡ (ወይም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት) ፡ ጕዳይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሐሳቦችና ፡ አስተያየቶች ፡ ይቀርቡበታል ። ]*

## ጦማረ ፡ ክዋኔ ፥ 3 ኛ ፦

# ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ እንመሥርት !

———

ሚያዝያ ፡ ቀን ፡ 2017 ፡ ዓ.ም. ።

ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድያ ፡ ዐላማ ፥ ሦስተኛው ፡ እና ፡ የመጨረሻው ፡ ረድፍ ፦

ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ እንመሥርት !

ይላል ።

### 4.1 ፤ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ኹነት ።

ከዐቢይ ፡ አንቀጽ ፡ "ነገሠ" ፥ መስም ፡ "መንግሥት" ፡ ይገኛል ፥ ይህም ፡ የንጉሥ ፡ መግዣ ፡ ወይም ፡ የንጉሥ ፡ አገዛዝ ፡ ማለት ፡ ነው ። ዛሬ ፡ ግን ፥ የንጉሥ ፡ ላልኾነ ፡ አገዛዝም ፡ መንግሥት ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ጸንቷል ። ሕዝብ ፡ የነገሠበት ፡ ሥርዐት ፡ ተክቶታል ፡ ብንል ፡ ደግሞ ፥ መንግሥት ፡ ሙሉ ፡ ትርጕሙን ፡ ያገኛል ።

በጦማር-2 ፡ ዘርዘር ፡ አድርገን ፡ እንዳየነው ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ (ወይም ፡ ዐምሐራ) ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ወይም ፡ ክዋኔውን ፡ በደምፁ ፡ ሲያጸድቅ ፥ ኹነቱን ፡ (ወይም ፡ በግእዝ ፥ ኩነቱን) ፡ በፈቃዱ ፡ ይከውናል ፥ መንግሥቱን ፡ ያቆማል ።

### 4.2 ፤ የኹነት ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ሦስቱ ፡ አካላት ፡ እና ፡ ሥልጣናቸው ።

ኹነት ፡ ወይም ፡ መንግሥት ፡ ሦስት ፡ አካላት ፡ አሉት ፥ እነሱም ፦

1ኛ ፤ **ሐጋጊው ፡ አካል** ፤ የሐጋጊው ፡ ሥልጣን ፡ ባለቤት ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ በሀገሩ ፡ ክዋኔ ፡ መሠረት ፥ የሀገርን ፡ ሕግጋት ፡ ኹሉ ፡ በሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንገድ ፡ ያግጋል ።

2ኛ ፤ **ፈታሒው ፡ አካል** ፤ የፍታሒው ፡ ሥልጣን ፡ ባለቤት ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ በሀገሩ ፡ ክዋኔ ፡ መሠረት ፥ የሀገርን ፡ ሕግጋት ፡ ኹሉ ፡ ይተረጕማል ፥ ሕግን ፡ ያስከብራል ።

3ኛ ፤ **ፈጻሚው ፡ አካል** ፤ የፈጻሚው ፡ ሥልጣን ፡ ባለቤት ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ በሀገሩ ፡ ክዋኔ ፡ መሠረት ፥ የሀገርን ፡ አስተዳደር ፡ ኹሉ ፡ ይፈጽማል ።

እነዚህ ፡ ሦስት ፡ የኹነት/የመንግሥት ፡ አካላት ፡ ወይም ፡ ሕዋሳት ፥ አንዱ ፡ በሌላው ፡ አንጻር ፡ በሥልጣን ፡ እኩል ፡ ኾነው ፥ አንዱ ፡ በሌላው ፡ ሥራ ፡ ሳይገባበት ፡ በተዓቅቦ ፡ ተጠባብቀው ፡ ኹነትን ፡ ሕያው ፡ እና ፡ ርትዓዊ ፡ ያደርጋሉ ።

### 4.3 ፤ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ እንመሥርት ፥ ወይም ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ ኹነታችንን ፡ እንከውን ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2017 ፡ ዓ.ም. ።

እንደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብነታችን ፣ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ ወይም ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ ኹነታችንን ፡ ለመመሥረት ፣ አስቀድሞ ፡ ሀገራዊ ፡ እግዚእናችንን ፡ ማስከበር ፡ እና ፡ ክዋኔያችንን ፡ (ሕገ ፡ መንግሥታችንን) ፡ ማጽደቅ ፡ እንዳለብን ፡ በቀደሙት ፡ ጦማሮች ፡ ገልጸናል ።

"የልጅ ፡ ለቅሶ ፡ መልሶ ፣ መልሶ" ፡ እንዲሉ ፣ ዋናውን ፡ የሀገር ፡ ባለቤትነት ፡ ግዴታችንን ፡ መወጣትን ፡ ትተን ፣ በእየዕለቱ ፡ በሚከሠቱ ፡ ድርሶች ፡ እና ፡ በሚፈጸሙ ፡ ግፎች ፡ ቈዝመን ፡ እና ፡ ተዘናግተን ፡ ብዙ ፡ የሥራ ፡ ዘመን ፡ ጠፍቶብናል ። አኹንም ፡ ቢኾን ፣ ጊዜያችን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ የጠፋ ፡ ነገር ፡ የለም ፤ ሀገራችንን ፡ ከመታደግ ፡ የሚከለክለንም ፡ ምድራዊ ፡ ኀይል ፡ የለም ። ዐላማችንን ፡ ከተረዳነው ፡ ወዲያ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የምንልበት ፡ ምንም ፡ ምክንያት ፡ አይኖርም ።

ለሀገር ፡ ህልውና ፡ የምትታገሉ ፡ በሀገር ፡ ውስጥም ፡ በውጭ ፡ ሀገር ፡ የምትገኙ ፡ ኢትዮጵያውያን-ሀገራውያን ፡ ኹሉ ፣ **ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፡ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችኹ ፡ ነውና ፣ ፈጥናችኹ ፡ እንድትተባበሩት ፡ በሀገር ፡ ፍቅር ፡ ጥሪያችንን ፡ እናስተላልፍላችኺለን ።

ይህን ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ ትግል ፡ የምንመራበትን ፡ ስልት ፣ **ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፦

"ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡
ሀገራዊ ፡ ቅያስ"

በተሠኘው ፡ ሰነዱ ፡ አጠናቅሮ ፣ ለሕዝብ ፡ ስሜት ፡ አቅርቧል ፣ ፈጥነን ፡ ሀገራችንን ፡ እንታደግበት ፡ !

---

ስለ**ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፡ አመሠራረት ፡ እና ፡ ስለ ፡ መሠረታውያን ፡ ደንቦቹ ፡ በቂ ፡ መረጃን ፡ ከመርበቢያው ፡ ከ ፦

www.slttunhzb.net

ማግኘት ፡ ይቻላል ።

ማንኛውም ፡ ኢትዮጵያዊ-ሀገራዊ ፡ የ**ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፡ የመብት ፡ አባል ፡ ነው ፤ በመብቱ ፡ መሥራትን ፡ ወይም ፡ አለመሥራትን ፡ የራሱ ፡ ምርጫ ፡ ይወስነዋል ።

---

የ**ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፡ ዐላማን ፣ ማለት ፣ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፦

1ኛ ፤ ሀገራዊ ፡ እግዚእናውን ፡ (ገዢነቱን) ፡ እንዲያስከብር ፤
2ኛ ፤ ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ እንዲሠራ ፤
3ኛ ፤ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥቱን ፡ እንዲመሠርት ፡ መታገል ።

የሚሉትን ፡ ሦስት ፡ ክፍሎች ፣ እንሆ ፣ በሦስት ፡ ጦማሮች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ አብራርተናቸዋል ።

በዝርዝር ፡ ለማጥናት ፡ የምትሹ ፡ ኹሉ ፣ እ**ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፡ መርበቢያ ፡ ላይ ፦

www.slttunhzb.net

ሙሉ ፡ መረጃን ፡ የሚሰጡ ፡ ሰነዶች ፡ አሉላችኹ ፤ በተለይ ፡ ደግሞ ፣ "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፡ ሥራው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፣ ብዙውን ፡ ጉዳይ ፡ በዝርዝር ፡ ዐትቶላችኺል ።

ለማንኛውንም ፡ ጥያቄ ፡ ወይም ፡ አስተያየት ፡ በቀጥታ ፡ ከኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መልስ ፡ ለምትሹ ፡ ደግሞ ፡ በእ-ጦማር ፡ አድራሻው ፡ በ ፦

sh1ⓗttomar.net

ልትጽፉለት ፡ ትችላላችኹ ።

[ ጦማሮቹ ፡ ኹሉ ፡ የሚጻፉት ፡ በትኽክለኛው ፡ የፊደል ፡ አጠነቃቀቅ ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፣ በተቻለ ፡ መጠን ፡ የፊደል ፡ ስሕተቶችን ፡ ለማስወገድ ፡ ሞክረናል ፣ ለዚህም ፡ **ዐውደ-ቀለም** ፡ የተባለው ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ መግበር ፡ (software) ፡ ረድቶናል ፤ እናንተም ፡ እንድትሠሩበት ፡ እናበራታችኺለን ።

መገኛው ፦

www.awde-qelem.net ፡ ነው ፣

በ Windows ፡ ምግባር ፡ (operating ፡ system) ፡ ላይ ፡ ይሠራል ። ]

---

<u>የቃላት ፡ መፍቻ ፤</u>

**ሀገር** ፤ በራሱ ፡ ሥልጣኔ ፡ የተሠራ ፣ እግዚእና ፡ ያለው ፡ ሐራ ፡ ግዛት ፡ (Civilisation-State) ።

**ሀገራዊ** ፡ ( ስም ) ፤ የሀገር ፡ ሠሪ ፣ የሀገር ፡ ባለቤት ፣ ዐምሐራዊ ፡ (citizen, *n.*)


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፣ 2017 ፡ ዓ.ም. ።

**ሀገራዊ** ፡ (ቅጽል) ፤ የሀገር ፥ ዐምሐራዊ ፡ (citizen, *adj.*)

**ሕዝባዊ-ፈረዳ** ፤ ውሳኔ-ሕዝብ ፡ (referendum)

**መርበቢያ** ፤ የመረብ ፡ ገጽ ፡ መነኛ ፡ (web site)

**ሥልጡን** ፤ ሥልጣን ፡ ያለው ፥ የብጤውን ፡ መብት ፡ አክብሮ ፡ የራሱን ፡ መብት ፡ የሚያስከብር ፥ ሥሉጥ ፡ (civil)

**ሥልጡንሕዝባዊ** ፤ የሥልጡንሕዝብ ፡ (democratic)

**ሥልጡንሕዝብ** ፤ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፥ የብጤውን ፡ መብት ፡ አክብሮ ፡ የራሱን ፡ መብት ፡ የሚያስከብር ፥ ሥሉጥ ፡ ሕዝብ ፡ (democrat)

**ሥልጡንሕዝብና** ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡ ወይም ፥ አንዱ ፡ የሌላ ፡ ብጤውን ፡ መብት ፡ በማክበር ፡ ወንፈል ፥ ጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ በሀገርነት ፡ ዐብሮ ፡ የሚኖርበት ፡ ሥልጡን ፡ ሥርዐት ፡ (democracy)

**ስያስ** ፤ ዘዴ ፡ (policy)

**ስያሳ** ፤ "ፖለቲካ" ፡ (politics)

**ስያሳዊ** ፤ "ፖለቲካዊ" ፡ (political)

**እግዚእና** ፤ ገገርነት ፡ (sovereignty)

**ኢትዮጵያዊ-ሀገራዊ** ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊነት ፡ ያለው ፥ ዐምሐራዊ ፡ (Ethiopian citizen)

**እ-ጦማር** ፤ እለቁጥሯዊ ፡ ወይም ፡ ንምራዊ ፡ ጦማር ፥ መልክት ፡ (e-mail)

**ከወነ** ፤ ኹነትን ፡ ወይም ፡ መንግሥትን ፡ ኾነ ፣ ተሠራ ፣ ተመሠረተ ፣ ቆመ ፣ ጸና ፡ (to be constituted)

**ከወነ** ፤ ኹነትን ፡ ወይም ፡ መንግሥትን ፡ ሠራ ፣ መሠረተ ፣ አቆመ ፣ አጸና ፡ (to constitute)

**ከዋኝ** ፤ የሚከውን ፣ አኳኝ ፡ (constituent)

**ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፤ የሀገርን ፡ ክዋኔ ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለማርቀቅ ፡ እና ፡ ለማጽደቅ ፥ በመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ወቅት ፥ በሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንገድ ፡ በሕዝብ ፡ የተሠየመ ፡ የተወካዮች ፡ ጉባኤ ፡ (constituent assembly)

**ክዋኔ** ፤ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ (Constitution)

**ኹነት** ፤ (በግእዝ ፥ ኩነት) ፡ ሀላዌ ፡ ያለው ፡ አካል ፥ መንግሥት ፡ (State)

**ዐምሐራ** ፤ ዐም ፡ = ፡ ሕዝብ ፥ ሐራ ፡ = ፡ ነጻ ፥ በተገናኝ ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ ፥ የሀገር ፡ ባለቤት ፥ እግዚእና ፡ ያለው ፥ የሀገር ፡ ሠሪ ፥ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ (citizenry)

**ዐምሐራዊ** ፡ ( ስም ) ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ የዐምሐራ ፡ አባል ፥ ሀገራዊ ፥ አገሬ ፡ (citizen, *n.*)

**ዐምሐራዊ** ፡ ( ቅጽል ) ፤ የዐምሐራ ፥ የሀገር ፡ (citizen, *adj.*)

**ጦማር** ፤ መልክት ፡ (mail ፡ ወይም ፡ post)


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2017 ፡ ዓ.ም. ።